# ጮክ ብሎ የማንበብ መምሪያ ለቤተሰቦች




**ስሜ ሴልያ ነው (My Name is Celia/Me llamo Celia): የሴልያ ክሩዝ ህይወት (The Life of Celia Cruz/la vida de Celia Cruz)**

*ደራሲ፤ ሞኒካ ብራውን (Monica Brown)*

*ሰዓሊ፤ ራፌል ሎፔዝ (Rafael López)*
**ይዘቶች፤** ችግር መፍታት፣ የቡድን ስራ

**የመጽሃፉ አጭር መግለጫ፤** በኩባ በመዘመር ያደገችው እና ወደ አሜሪካ ከሄደች በኋላ ታዋቂዋ "የሳልሳ ንግስት" የሆነችው የሴሊያ ክሩዝ ደማቅ እውነተኛ ታሪክ!

## ጮክ ብለው ያንብቡ

**ከንባብ በፊት፤ ዳራ ይገንቡ (Build Background)**

- “ምን ዓይነት ሙዚቃ ማዳመጥ ትወዳለህ? ምን እንዲሰማህ ያደርጋል?” በማለት ይጠይቁ
- ይህ ታሪክ ኩባ ስለነበረችው ሴሊያ ክሩዝ (Celia Cruz) ስለምትባል እውነተኛ ዘፋኝ እንደሆነ ለልጅዎ አስረዱት ሙዚቃን በጣም ስለምትወደው ሳልሳ የሚባል አዲስ የሙዚቃ አይነት እንዲፈጠር ረድታለች። ይህ መጽሐፍ በእንግሊዝኛ እና በስፓኒሽ የተጻፈ መሆኑን ልብ ይበሉ።

**በንባብ ወቅት፤ ግንኙነቶችን ይፍጠሩ**

- ሴልያ (Celia) መስራት የምትወደው ነገር ምንድነው? ሙዜቃ እንዴት እንዲሰማት ያደርጋታል?
- የሴልያ (Celia’s) ህይወት ወደ አዲስ ቦታ ስትሄድ እንዴት ይለወጣል?
- ሴልያ (Celia) ለመፍጠር የረዳችውን ሙዚቃ ይግለጹ። ሳልሳ ሙዚቃ ምን ይመስላል?

**ከንባብ በኋላ፤ ጥያቄዎች ይጠይቁ**

- “ሴላ ክሩዝ ሙዚቃ መውደዷን ለዓለም ያካፈለችው እንዴት ነው? ፍላጎታችንን ስለመከተል የእሷ ታሪክ ምን ያስተምረናል?“ በማለት ይጠይቁ።

## ተዛማጅ ተግባራት

**ልጅዎ ይህንን መጽሃፍ ከወደደው፤**

- “የሳልሳ ሙዚቃ ፓርቲ (Salsa Music Party)“ ያዘጋጁ። የሳልሳ ሙዚቃ ወይም ሌላ ዓይነት ባህላዊ ሙዚቃ እያዳመጣችሁ አብራችሁ ደንሱ! ልክ እንደ ሴሊያ ክሩዝ በሃይል እና በደስታ እንዳከናወነች ልጅዎን ወደ ሪትም እንዲሄድ እና የተለያዩ መሳሪያዎችን እንዲያስተውል ያበረታቱት።
- በ አር አይ ኤፍ (RIF) ውስጥ ተጨማሪ የሁለት ቋንቋ ጽሑፎችን ያስሱ፤ የስፓኒሽ ቋንቋ ስብስብ (Spanish-Language Collection)።


©2025 Reading Is Fundamental